# የዘመናት ወዝግብን የገታ አገራዊ ጥረት

ማሕመድ ናስር

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ያወጣው አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው በመላው ዓለም 263 የሚሆኑ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችና ሌሎች ተፋሰሶች ይገኛሉ፡፡ እያንዳንዱን ተፋሰስ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አገራት ይጋራሉ፡፡ የምንኖርባት ሜሬትን በግማሽ የሚሸፍኑት እነዚህ ተፋሰሶች ከጠቅላላው የዓለም ህዝብ መካከልም 40 በመቶ ከሚሆነው ህይወት ጋር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የተቆራኙ መሆናቸውን ሰነዶች ያስረዳሉ፡፡

እስካሁን ድረስ ተፋሰሶችን በሚጋሩ አገራት መካከል ከኃብቱ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ አንድም ጊዜ ጦርነት ያልተከሰተ ቢሆንም ተፈጥሯዊ ኃብቱን በጋራ ከማጠቀም፣ ከማስተዳደርና ከማጠበቅ አንፃር በአንዳንድ አካባቢዎች አሁንም ድረስ አለመግባባቶች እንዳሉ ይነገራል፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን በወሃ ኃብቱ አጠቃቀም ዙሪያ ባለፉት 50 ዓመታት ጊዜ ወስጥ የተስተዋለው መግባባትና የጋራ ትብብር መንፈስ በከፍተኛ ማጠን እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

በጥናቶች ማስረት በተጠቀሰው ጊዜ ወስጥ ከ150 በላይ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በሚገለከታቸው የተፋሰሱ አባል አገራት መካከል ተፈርመው ስራ ላይ ወለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወስጥ የተስተዋሉት የአለመግባባት ክስተቶች ግን 37 ያህል ብቻ ናቸው፡፡

አብዛኛዎቹ እነዚህ ስምምነቶት የየአገራቱን ህዝቦች ግንኙነት ከማቁራኘት አኳያ በመጫወት ላይ የሚገኙት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ስምምነቶቹ የፖለቲካ አስተሳሰብ ድንበርን ተሻግረው ከሰብአዊነት ጋር ፍፁም ቁርኝትን መፍጠር የተቻለበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ የጋራ ተፋሰስ ባላቸው አንዳንድ አገራት መካከል የተፈረሙ ስምምነቶች በአገራቱ

ዘንድ በሌላ ፖለቲካዊ አለመግባባት ሳቢያ በተከሰቱ ጦርነቶች እንኳ ሳይቀለበሱ እስካሁንም ድረስ ፀንተው መዝለቃቸውን የታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ፡፡

ለዚህም እንደአብነት ሊነሱ ከሚችሉት የተለያዩ አገራት መካከል አሁንም ድረስ ባልተፈታ የፖለቲካ ውዝግብ ወስጥ የሚገኙት ህንድና ፓኪስታን ያቋቋሙትና The Indus River Commission የሚሰኘው ስምምነት ይጠቀሳል፡፡ ይህ የእነዚህ አገራት ስምምነት የፈጠረው ኮሚሽን አገራቱ በተለያዩ ሁለት ወቅቶች ባካሄዷቸው ጦርነቶች ሳይቀለበስ እንደፀና ቆይቷል፡፡

የዮርዳኖስ ወንዝን የሚጋሩት እስራኤልና ዮርዳኖስም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል ታሪክ አላቸው፡፡ እነዚህ አገራት በፖለቲካ ውዝግብ ወስጥ ያሉ አገራት ቢሆኑም በጋራ የተፈጥሮ ኃብታቸውን በፍትሃዊ መንገድ ማጠቀም በሚችሉበት መንገድ ዙሪያ የሚካሄዱትን ወይይት ሳያቋርጡ የቀጠሉበት ሁኔታ መኖሩን ሰነዶች ያመለክታሉ፡፡

እነዚህ ክስተቶች አገራት የሚጋሯቸው ወንዞችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለማጠቀም የሚያስችሏቸውን ተቋማዊና ህጋዊ ስርዓትን ለማበጀት በቅን ልቦና ከተነሳሱ ከግጭት ይልቅ የሚጠበቁትን ዓይነት ጠንካራ የትብብር ግንኙነት መፍጠር እንደሚችሉ የሚያረጋግጡ እወነቶች ናቸው፡፡ በተለይ የዓለም ህዝብ ቁጥር በእጅጉ እየጨመረና የህዝቦች ወሃን የመሳሰለ የተፈጥሮ ኃብት ፍጆታ እያደገ በመጣበት በአሁኑ ወቅት ወይይትና ትብብር ቁልፍ መሆኑን ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ምሁራን በአፅንኦት የሚሰጡት ምክር ነው፡፡

በአጠቃላይ በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ላይ የሚካሄድና የአገራት የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያላደረገ ተግባር በምንም ሚዛኑ የሚያዋጣ ከወንዙ ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል መሆኑም በብዙ ምሁራን ተቀባይነትን ያገኘ ሀቅ እየሆነ መጥቷል፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ሰጠኝ ያህል አገራት የሚጋሩትን የአባይ ወንዝ ሁሉም የተፋሰሱ አባል አገራት በፍትሃዊነት ማጠቀም የሚችሉበትን መንገድ ለማመቻቸት የተጀመረው የትብብር ጥረት ይጠቀሳል፡፡ የተፋሰሱ አባል አገራት ይህንን ትልማቸውን እውን

ሚያደርግ ይችሉ ዘንድ የአባይ ተፋሰስ የትብብር መድረክ (Nile Basin Initiative) የተሰኘ መድረክ ማስርተዋል፡፡

የአባይ ወንዝ ውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ ሁሉንም የተፋሰሱ አባል አገራት ያካተተ ዓለም አቀፍ ስምምነት የለም፡፡ ለብዙ አስርት ዓመታት የሚጠቀሰው ስምምነት ግብጽና ሱዳንን ብቻ ተጠቃሚ እያደረገ የሚገኘውና በአውሮፓዊያን የዘመን አቆጣጠር በ1959 የአገራቱ ቀኝ ገዢ በነበረችው እንግሊዝ አማካኝነት የተፈረመው ስምምነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሌሎቹን የተፋሰሱ ተጋሪዎች ተፈጥሮአዊ መብት ጣሉ በጣሉ የገደበ በመሆኑ በአገራቱ ተቀባይነት ሳያገኝ ለብዙ ዓመታት ኖሯል፡፡

በዚህ ምክንያት ነው ኢትዮጵያን ጨምሮ የተፋሰሱ አባል አገራት ከወንዙ ሊያገኙ የሚገባቸውን ህጋዊና ፍትሃዊ ጥቅም ለሚያረጋገጥ ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኙት፡፡ በወንዙ ተጋሪ አገራት ወስጥ የሚከሄዱትን የኢኮኖሚ ልማት ጥረቶች በማፋጠን በአካባቢው እድገትን ለማምጣት የሚያልመው ይህ ዓመታትን የወሰደው የአባይ ተፋሰስ አባል አገራት ወይይትና ድርድር ወጤት ማስየት ጀምሯል፡፡ ይህንንም ተከትሎ ኢትዮጵያና አምስት የተፋሰሱ አባል አገራት ወንዙን በፍትሃዊነት ማጠቀም የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር እንደ አወሮፓ አቆጣጠር በ2010 አንድ የትብብር ማእቀፍ ውል (Cooperative Framework Agreement) ፈርመዋል፡፡

ስምምነቱን እስካሁን ያልፈረሙት ግብፅና ሱዳን በሰነዱ ላይ ጥርጣሬ አድሮባቸዋል፡፡ የእነዚህ አገራት ዋነኛው ስጋት ስምምነቱ የወንዙን ተጠቃሚነታቸውን ይጎዳዋል የሚል እንደሆነ ይነገራል፡፡

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳንን ካቀፈውና የምስራቃዊ አባይ ተፋሰስ ክፍለ አህጉራዊ የቴክኒክ ቢሮ (Eastern Nile Technical Regional Office) ከተሰኘው ተቋም ላለፉት ሁለት ዓመታት ተገለው ቆይተዋል፡፡ በሶስቱ አገራት ስምምነት የተከፈተው ቢሮ አገራቱ የአባይ ወንዝን ውሃ በዘላቂነት ለማስተዳደር፣ በፍትሃዊነት ለማጠቀምና ለማልማት በሚቻልበት መንገድ በጋራ የሚመክሩበት ነው፡፡

ሆኖም ግን ሁለቱ አገራት በዚህ ሰሞን ቢሮውን በመቀላቀል ከኢትዮጵያ በጋራ ለመስራት ወስነዋል፡፡ ጉዳዩን በቅርበት የሚያውቁ ታዛቢዎች እንደሚሉት ይህ የግብፅና ሱዳን ውሳኔ የሚያሳየው አገራቱ ከውዝግብ ይልቅ ውይይትንና ድርድርን ማምረጣቸውንና የተፋሰሱ አባል አገራት ወንዙ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ሁሉንም ተጠቃሚ ለማድረግ የጀመሩትን ጥረት የሚቀበሉ መሆናቸውን ነው፡፡

ይህ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ጊዜ የፈጀው ድርድር አሁን ለደረሰበት የሚያበረታታ ውጤት እንዲበቃ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና የላቀ መሆኑን ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ አካላት ይገልፃሉ፡፡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትም ሂደቱ በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የቆየውን ውዝግብ በሚገባ በአገራቱ መካከል ጠንካራ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ግንኙነትን ለመፍጠር የሚያስችል መሰረት መሆኑንም ይመሰክራሉ፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝ የሚመነጭባት ብቸኛዋ አገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ወንዙ የተቀሩት ዘጠኝ አገራት ኃብት መሆኑንም ያለምንም ማወላወል ትቀበላለች፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በወንዙ እየተጠቀሙ ለሚገኙት ግብፅና ሱዳን ህዝቦች የምትጠሰው ትኩረት የላቀ መሆኑን ከተለያዩት የአገሪቱ መንግስት ባለስልጣናትና እየተወሰዱ ከሚገኙት ተግባራዊ እርምጃዎች መረዳት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ የአባይ ወንዝ ፍትሃዊ አጠቃቀም ስርዓት እንዲበጅለት እያደረገች ያለው ጥረትና የህዳሴው ግድብ ግንባታን የጀመረችው የሌሎችን ጥቅም አለመንካትና ጉዳት አለማስከተል እንደዚሁም ተጠቃሚነትን ሚረጋገጥ የሚሆኑን ዓለም አቀፍ የውሃ አስተዳደር ህግጋትን በማንተራስ ነው፡፡

ይህ የኢትዮጵያ መንግስት የጋራ ተጠቃሚነት መርህ በተለይ ግንባታው እየተካሄደ በሚገኘው በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ላይ በስፋት ተንፀባርቋል፡፡ የህዳሴው ግድብ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ መንግስት የሚያካሄደው ዲፕሎማሲያዊ ጥረት የሚመለከታቸውን አካላት ጭምር ያስደመመ ነው፡፡ ግድቡን በተመለከተ በግብፅና ሱዳን ዘንድ የተፈጠረውን የተሳሳተ ግንዛቤና አላስፈላጊ ስጋት ለማስወገድ የኢትዮጵያ መንግስት እየተከተለው ያለው የውይይትና የትብብር መንፈስ በብዙዎች ተቀባይነትን አትርፏል፡፡

መንግስትና የአገሪቱ የውሃ ባለሙያዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደገለፁት የህዳሴው ግድብ የግብፅንም ሆነ የሱዳንን ህዝቦች ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል አይደለም፤ የአገራቱ የውሃ ድርሻንም በምንም መልኩ ሊገዳ አይችልም፤ ይልቁንም አገራቱ ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ መልኩ የግድቡ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

አገሪቱ የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያ ውስጥ በሊዝ መሬት ወስደው በሚንቀሳቀሱ ኩባንያዎች የማስኖ እርሻ አገልግሎት እንደሚይውል በተደጋጋሚ ቃል ገብታለች፡፡ በኢትዮጵያ ተነሳሽነት ግድቡ የግብፅንና ሱዳንን ጥቅም የሚነካ መሆንና አለመሆኑን በማጥናት ሪፖርት የሚያቀርብ ሶስቱን አገራት የሚያካትት ዓለም አቀፍ የቴክኒክ ቡድን ተዋቅሮ ስራውን መጀመሩም ኢትዮጵያ ለሌሎቹ የተፋሰሱ አገራት ያላትን ተቆርቋሪነት ያሳየ ታላቅ የዲፕሎማሲ ጥረት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡

በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ በምንም መልኩ ሌሎችን የመጉዳት ሀሳብ እንደሌላት በተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላትና ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎች ጭምር እየተረጋገጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ሊጠቀስ የሚችለው ትልቅ ማስያ አለም አቀፉ የውሃ አስተዳደር ተቋም ከሁለት ሳምንታት በፊት ይፋ ያደረገው አዲስ ጥናት ነው፡፡ ተቃሙ የአባይ ወንዝ ለአስሩም የተፋሰሱ አገራት በቂ ውሃ መኖሩን በጥናት ሚረጋገጡ ከላይ የተጠቀሰውን የኢትዮጵያ አቋም የሚያጠናክር ነው፡፡

ኢትዮጵያ እያራመደችው ያለው እውነተኛ የትብብር መንፈስ የግብፅንና ሱዳንን መንግስታትና ምሁራንን ጭምር ማስመን ጀምሯል፡፡ እነዚህ አካላት እየሰጡት ባለው አስተያየት ማስረት የህዳሴው ግድብ በምክክርና መግባባት መርህ እውን ከሆነ ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ ግብጽንና ሱዳንን እጅግ ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የሱዳን የውሃ ባለሙያዎች ግብፅና ሱዳን ከህዳሴው ግድብ የሚመነጨውን የኤሌክትሪክ ኃይል በአነስተኛ ዋጋ እንዲጋሩ የሚያስችላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ግንባታው በአባይ ወንዝ አማካኝነት ግብጽንና ሱዳንን ለዘመናት ለጉዳት ሲዳርግ የኖረውን የደለል

ክምርና እርሱንም ተከትሎ ይፈጠር የነበረውን የጎርፍ አደጋ እንደሚያስወግድ አረጋግጠዋል፡፡

ሚዲያዎች እንደሚጠቁሙት ከአባይ ወንዝ ጋር በተያያዘ በግብፅና ሱዳን የሚፈጠረውን ደለል ለማስወገድ በየጊዜው አገራቱ ከፍተኛ ወጪ ያወጣሉ፡፡ የህዳሴው ግድብ ይህንን ወጪ ያስቀራል፤ በወንዙ ዳርቻ የሚኖሩትን የሁለቱን አገራት ህዝቦችንም ከጎርፍ አደጋ ይታደጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ግድቡ የወንዙን የውሃ ማጠን በማስደግ ረገድም ትልቅ አስተዋፅኦ እንዳለው ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት በወንዙ ውሃ ትነት አማካኝነት በተለይ በታችኛው የተፋሰሱ አገራት ዘንድ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የውሃ ብክነት ችግር የህዳሴው ግድብ ያስወግደዋል፤ ይህንንም ተከትሎ የወንዙ የውሃ ማጠን ይጨምራል የሚል እምነት አለ፡፡

በግብፅ መንግስትና ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎችም ይህንን የሚደግፉ አስተያየቶች በመቅረብ ላይ ናቸው፡፡ ግብፅን በሽግግር መንግስትነት የመሩት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳም ሸሪፍ የህዳሴው ግድብ በሶስቱ አገራት የሚካሄዱትን የልማት ጥረቶች በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፤ ግድቡ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ግብፅንና ሱዳንንም ይጠቅማል በማለት ገልፀዋል፡፡

አዲሱ የግብፅ መንግስትም ሰሞኑን እንደገለፀው የህዳሴው ግድብን ጨምሮ በአባይ ወንዝ ዙሪያ የግብፅ ባለሥልጣናትና ሌሎች ግለሰቦች በተለያዩ ሚዲያዎች የሚሰጡት መግለጫ የግብፅ መንግስት አቋም ፈጽሞ እንደማያንፀባርቅ ሚጋገጠም አገሪቱ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር ለመስራት ያላትን ዝግጁነት የሚያሳይ ነው፡፡

የግብጽ የውሃ ሀብትና የመስኖ ሚኒስትር ባለፈው ሳምንት ለአንድ የአገሪቱ ጋዜጣ የሰጡት መግለጫም ይህንን የግብፅ ዝግጁነት ያሳያል፡፡ ሚኒስትሩ የላይኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች የግብጽ የውሃን ድርሻ የሚይነካ እስከሆነ ድረስ የሚፈልጉትን ግድብ

ቢገነቡ የግብጽ መንግስት አይቃወምም በሚለት ሚስታወቃቸው ሌላው የግብፅን ለትብብር ማዘጋጀት የሚያመላከት እርምጃ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ በግብጽ ላይ የውሃ እጥረት እንዳያስከትል የሚያስችል ፕሮጀክት ለማቋቋም የኢትዮጵያ መንግስት ዝግጁ መሆኑን እኚሁ የግብፅ ባለስልጣን ጠቁመዋል፡፡ በአባይ ወንዝ ያለውን ውሃ ለሁሉም የአባይ ተፋስ ሀገሮች የወደፊት ፍላጎት እንዲበቃ ለማድረግ በጋራ መንቀሳቀስ የግድ ነው፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ጋር የትብብር ግንኙነት ይፈጠራል ብለዋል፡፡

በሳዳት የስልጣን ዘመን የግብፅ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩትና በኋላ ላይም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ በመሆን ያገለገሉት ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ Egypt's Road To Jerusalem – a diplomat's story of struggle for peace in the middle East በተሰኘው መፅሃፋቸው በአባይ ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነትን ከሚረጋገጥ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

የሱዳን መንግስት ባለስልጣኖትም የህዳሴው ግድብ ለሱዳን ህዝብ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ዓይነተኛ ፕሮጀክት መሆኑን በመግለፅ ለግንባታው ስኬት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ በሱዳንና ግብጽ ላይ ያለው አዎንታዊ ተፅዕኖ በሚል ርዕስ ባለፈው ሳምንት ካርቱም ወስጥ በተካሄደው አወደ ጥናት ላይ የተካፈሉት የአፍሪካ ዓለማቀፍ ዩኒቨርሲቲ አማካሪ ፕሮፌሰር ሐሰን መኪ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 50 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ በማያዝ በአፍሪካ ትልቁ ሰው ሰራሽ ሐይቅ ይፈጥራል፤ ይህም ለሱዳን የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ይሆናል ብለዋል፡፡ የሱዳን የግብርና ሚኒስቴር አማካሪ አህመድ መሀመድ አደም በበኩላቸው ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን በትብብር መስራት አለባቸው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በተመሳሳይ የሱዳን የውሃ ሀብት ባለሙያ ሰይፈዲን ሀመድ በኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ሱዳንና ግብጽ በኤሌክትሪክ ኃይልና በግብርና ልማት ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የትብብርና የመተማመን መንፈስ ለመፍጠር የጀመረውን ይህንን ጥረቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ የህዳሴ ግድብ በዓባይ ወንዝ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያስከትል ለግብፅ የሚያስረዳ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተወጣጡ አባላትን ያካተተ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥትን በመወከል ወደ ግብፅ ለመላክ ማዘጋጀቱን ሰሞኑን ይፋ አድርጓል፡፡

ከዩኒቨርሲቲ ምሁራን፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከመገናኛ ብዙኀን፣ ከሥነ ጥበብና ከእምነት ሜዎች የተወጣጡ የዲፕሎማሲ ቡድን ወደግብፅ የሚጓዘው ግብፃዊያን አትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ምክንያት ትጐዳናለች በሚል ይዘውት የቆዩትን የተሳሳተ እምነት በበለጠ ደረጃ ለመቀየር ነው፡፡

ዓባይን ገድቦ የግብፅ ሕዝብን መጉዳት በሰው ልጅ ሰብዓዊነት ላይ ወንጀል ሚፈጸም መሆኑን የሚያምነው የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይም ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ በተሳሰረው የግብፅ ሕዝብ ላይ ጉዳት ለፈጽም ፈጽሞ እንደሚይፈልግ ለግብፅ ህዝብ ማስረዳት የቡድኑ ዋነኛ ግብ ነው፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሶስቱ አገራት መካከል በጋራ ለማሰራት የሚያስችል ከፍተኛ ፍላጎት ተፈጥሯል፡፡ ግብፅና ሱዳንም የህዳሴው ግድብ የሶስቱ አገራት ህዝቦች የጋራ ኃብት ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ማመን ጀምረዋል፡፡

ይህ መልካም ወጤት ኢትዮጵያ ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ የምትከተለው የውጭ ፖሊሲ ወጤት ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ አገሪቱ በተለይ የቅርብ ጎረቤቶቿ ሰላምና እደገት ለራሷም ጭምር የሚጠቅማት መሆኑን በትክክል በማንዘብ ነው ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የጀመረችው፡፡

የህዳሴው ግድብም የሶስቱ አገራት መንግስታትን ብቻ ሳይሆን ህዝቦችን ጭምር ለማቀራረብ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ የአገራቱን የኢኮኖሚ ፖለቲካ ትብብርንም የበለጠ እንደሚያጠናክረው በብዙዎች ይታመናል፡፡

የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለዘመናት የኖረወን ወዝግብ ከሚፐገብ አኳያ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ መሆኑን ማንዘብ አያዳግትም፡፡ የአባይን ወሃ በወይይትና በትብብር በጋራ ሚልማት ሁሉንም የተፋሰሱ አገራት ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚቹል ማባባት መፍጠር የተቻለወም በዚሁ በአገሪቱ የበሰለ የዲፕሎማሲ ጥረት አማካኝነት ነው፡፡